የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፯ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 8
ADDIS ABABA 26th December, 2014

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፷፱/፪ሺ፯ ዓ..ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በማላዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገ የኢኮኖሚ፣ የንግድ፣ የባህል እና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……………………………………………………ገጽ ፯ሺ፱፻፭

## CONTENTS

Proclamation No. 869/2014

The Economic, Trade, Cultural and Technical Co-operation Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopian and The Government of the Republic of Malawi Ratification Proclamation ……………………………………………Page7905

### አዋጅ ቁጥር ፰፻፷፱/፪ሺ፯

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በማላዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የኢኮኖሚ፣ የንግድ፣ ባህል እና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በማላዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገ የኢኮኖሚ፣ የንግድ፣ የባህል እና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት እ.አ.አ ጃኑዋሪ ፳፯ ቀን ፪ሺ፯ አዲስ አባባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵየ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION No. 869/2014

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE ECONOMIC, TRADE, CULTURAL AND TECHNICAL CO-OPERATION AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMET OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMET OF THE REPUBLIC OF MALAWI

WHEREAS, the Economic, Trade, Cultural and Technical Co-operation Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Malawi was signed in Addis Ababa at the session held on the 27th day of January, 2007;

WHEREAS, the House of the People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 13th day of November 2014.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 9.50

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80,001

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በማላዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገ የኢኮኖሚ፣ የንግድ፣ የባህል እና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፷፱/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በማላዊ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል እ.አ.አ ጃኑዋሪ ፳፯ ቀን ፪ሺ፯ በአዲስ አበባ የተፈረመው የኢኮኖሚ፣ የንግድ፣ የባህል እና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ይህንን ስምምነት በሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፯ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዝዳንት

1. <u>**Short Title**</u>

This Proclamation may be cited as the "The Economic, Trade, Cultural and Technical Co-operation Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopian and The Government of the Republic of Malawi Ratification Proclamation No.869/2014".

2. <u>**Ratification of the Agreement**</u>

The Economic, Trade, Cultural and Technical Co-operation Agreement signed in Addis Ababa on the 27th day of January, 2007 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Malawi is hereby ratified.

3. <u>**Power of the Ministry of Finance and Economic Development**</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is here by empowered to implement this agreement.

4. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 26th day of December,2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት